የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| ፳ኛ ዓመት ቁጥር ፲<br>አዲስ አበባ ጥር ፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም. | በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 20th Year No. 10<br>ADDIS ABABA 15th January 2014 |
|---|---|---|

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፩/፪ሺ፮ ዓ.ም.

የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............. ገጽ ፯ሺ፩፻፸፭

CONTENTS

Regulation No. 301/2013

Ethiopian Public Health Institute Establishment Council of Ministers Regulation........................................ Page 7175

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፩/፪ሺ፮

## የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፭ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፩/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "ምርምር" ማለት አዕምሯዊ እውቀትን በመ ጠቀም አዲስ ነገር ለማግኘት፣ ዘዴዎችንና አሰራሮችን ለመፍጠር፣ ለመተንተን የሚደረግ ጥናት ሲሆን የሰው ልጆችን እውቀት በማጎልበት የጤና ችግሮችን የሚፈታና ኑሮን የሚያሻሽል እንቅስቃሴ ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 301/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN PUBLIC HEALTH INSTITUTE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 35 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended by Proclamation No. 803/2013).

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Public Health Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 301/2013".

### 2. Definitions

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "research" means a public activity based on intellectual application to investigate matter, to discover, interpret and develop methods and systems for the advancement of human knowledge, to solve health problems and improve life;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.20

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

፪/ "የቴክኖሎጂ ሽግግር" ማለት በኢንዱስትሪዎች፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ በመንግሥትና በሌሎች ተቋማት መካከል የሚደረግ የሙያ፣ የእውቀት፣ የቴክኖሎጂ፣ የአመራረት ዘይቤዎችን፣ የምርት ናሙናዎችን የመለዋወጥ ሂደት ሆኖ በውጤቱም ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ እድገቶች ለተጠቃሚ የሚደርስበትና ተጠቃሚውም ቴክኖሎጂውን ወደ አዲስ ምርት፣ ሂደት፣ ጥቅም፣ ቁሳቁስ ወይም አገልግሎት የሚቀይርበት ሂደት ነው፤

፫/ "በስርዓተ ጤና ላይ የሚደረግ ምርምር" ማለት የህክምና አገልግሎት አሰጣጥን፣ የህክምና መሳሪያዎችና መድሃኒቶችን አቅርቦት፣ የሰው ኃይል ሥልጠናና አመዳደብ፣ የበጀት አመዳደብና አጠቃቀም፣ የጤና መረጃ ስርዓትን፣ የጤናውን ዘርፍ ፖሊሲና አስተዳደር በተመለከተ የሚደረግ ችግር ፈቺ ጥናት ነው፤

፬/ "ድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር" ማለት የህብረተሰብ ጤና ችግሮችን ለመቀነስ የሚደረግ የጤና ቅኝት፣ የመተንበይ፣ አደጋውን የመለየት፣ የመከላከል፣ የመዘጋጀት፣ ተገቢ ምላሽ የመስጠት፣ የመቆጣጠርና ከህብረተሰብ ጤና አደጋ ተፅኖ ቶሎ የማገገም ሂደት ነው፤

፭/ "ሪፈራል ዲያግኖስቲክ ምርመራ" ማለት በሌላ ላብራቶሪ ሊሠራ የማይችል የምርመራ ዓይነት ወይም በሌላ ላብራቶሪ ተሠርቶ ተጨማሪ ማረጋገጫ የሚሻ የምርመራ ዓይነት ነው፤

፮/ "ሪፈራል አናሊቲካል ምርመራ" ማለት ከሌላ የምግብ፣ የውሃና የአካባቢ ናሙና ምርምራ ላብራቶሪዎች አቅም በላይ የሆነና ተጨማሪ የጥራት ማረጋገጫ የሚፈልግ የምርመራ ዓይነት ነው፤

፯/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

2/ "technology transfer" means the process of sharing of skills, knowledge, technologies, methods of manufacturing samples and facilities among industries, universities, government and other institutions to ensure scientific and technological developments are accessible to a wider range of users who can then develop and exploit the technology into new products, processes, applications, materials or services;

3/ "health system research" means a problem solving study undertaken on health service delivery, medical equipment and drug supply, human resource training and deployment, budget allocation and utilization, health information and management system and health sector policy and governance;

4/ "public health emergency management" means the process of conducting health surveillance, anticipating, detecting, preventing, preparing for, responding to, and recovering from consequences of public health threats in order that health risks are minimized;

5/ "referral diagnostic test" means a laboratory test that cannot be performed in another laboratories or a test that is within the competence of other laboratories but needs further confirmatory test;

6/ "referral analytical test" means a laboratory test that is beyond the capacity of other food, water and environmental laboratories or a test that is within the competence of such laboratories but needs further confirmatory test;

7/ "region" means any state referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

፰/ "ሚኒስቴር" ማለት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነው፤

፱/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. <u>መቋቋም</u>

፩/ የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

## ፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

## ፭. <u>የኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በአገር አቀፍ የህብረተሰብ ጤና ምርምር አጀንዳ ላይ ተመሥርቶ ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው የጤናና ሥነ ምግብ ችግሮች ላይ ምርምር ማድረግ እና ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ እውቀትን በማመንጨት፣ በመቅሰምና በማሰራጨት የህብረተሰቡን ጤና ማሻሻል፤

፪/ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ቅኝት በማካሄድ ስጋቶችን ቀድሞ መለየትና በቂ ዝግጅት በማድረግ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ በተገቢ ሁኔታ መከላከል፣ ሲከሰትም ማንቂያ፣ ማስጠንቀቂያና ወቅታዊ መረጃ ማስተላለፍ፣ ፈጣንና ብቁ ምላሽ መስጠት እንዲሁም የተጎዳውን የህብረተሰብ ክፍል ከጤና አደጋው ተጽኖ በፍጥነት እንዲያገግም ማድረግ፤

፫/ የኢንስቲትዩቱን ላብራቶሪዎችን በሰለጠነ የሰው ኃይልና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ በማጠናከር ችግር ፈቺ ምርምሮችን ማካሄድ፣ ለህብረተሰብ ጤና አደጋ ውጤታማ ምላሽ መስጠት፣ ሪፈራል ዲያግኖስቲክና አናላቲካል ምርመራዎችን ማካሄድ፤ በአገር አቀፍ ደረጃ የጤናና የምግብ ሳይንስ ላብራቶሪዎችን አቅም በመገንባት ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፡፡

8/ "Ministry" means the Ministry of Health;

9/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. <u>Establishment</u>

1/ The Ethiopian Public Health Institute (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

## 4. <u>Head Office</u>

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

## 5. <u>Objectives of the Institute</u>

The Institute shall have the objectives to:

1/ undertake research, based on national public health research agenda, on priority health and nutrition problems, and generate, absorb and disseminate scientific and technological knowledge to improve the health of the general public;

2/ in collaboration with the concerned bodies, conduct surveillance for the early identification and detection of public health risks and prevent public health emergencies through adequate preparedness; and alert, warn and dispatch timely information during public health emergency, respond effectively and timely and ensure rapid recovery of the affected population from the impact of the public health emergency;

3/ strengthen its laboratories with trained man power and technology to undertake problem solving researches, provide effective response to public health emergencies, carry out referral diagnostic and analytical tests; and support the capacity building of health and food science laboratories at the national level to enable them provide quality laboratory services.

፮. <u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የህብረተሰብ ጤናና ሥነ ምግብን በተመለከተ አገራዊ የምርምር አጀንዳ ይቀርጻል፣ በአጀንዳው ላይ የተመረኮዘ ምርምር ያካሂዳል፣ በተገኙ የምርምር ውጤቶች ላይ ተመርኩዞ የፖሊሲ ሐሳብ ያቀርባል፣ የምርምር ውጤቶችን ያሰራጫል፣ የተሰሩ ምርምሮችን ፋይዳ ይገመግማል፤

፪/ በአገሪቱ ውስጥ የሚከናወኑ ምርምሮች የሚቀናጁበትና ውጤታማ የሚሆኑበት አሰራር ይዘረጋል፣ አገር አቀፍ የምርምር መረጃ ቋት ይመሰርታል፣ ክልሎችና ሌሎች ተቋማት ለሚያከናውኗቸው ምርምሮች ድጋፍ ይሰጣል፤

፫/ ለህብረተሰቡ ዋና ዋና የጤና ችግሮች የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማስረጽ ክትባትን፣ የበሽታ መመርመሪያ ኪቶችን፣ የምግብ ሳይንስና ሥነ ምግብ ምርምር ውጤቶችን እና ሌሎች ለጤና አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶችንና ውጤቶችን እንደአስፈላጊነቱ ያመርታል ወይም በአገር ውስጥ በስፋት እንዲመረቱ ሳይንሳዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

፬/ በስርዓተ ጤናውና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ምርምሮች እና ግምገማዎችን በማድረግ በሽታን ለመከላከል እና ጤናን ለማበልፀግ የሚደረገውን ጥረት ያግዛል፤

፭/ የአካባቢና የሥራ ቦታ ደህንነትና ጤና መሠረት ያደረጉ የህብረተሰብ ጤና ምርምሮች ይሰራል፤

፮/ በተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች፣ በሥነ ምግብ፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ በጤና ሥርዓቱ ላይ እና በሌሎች መሰል የጤና ጉዳዮች ላይ አገራዊ ዳሰሳና ቅኝቶችን ያካሂዳል፤

፯/ የምግብ እጥረትና ያለመመጣጠን የሚያስከትሏቸው በሽታዎች የሚወገዱበትን መንገድና በቤተሰብ ደረጃ የአመጋገብ ሁኔታ እንዲሻሻል የሚያስችል ምርምር ያካሂዳል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፤

፰/ በባህል መድሃኒቶችና ሕክምና ዘዴዎች እንዲሁም በዘመናዊ መድሃኒቶች ላይ ምርምር ያካሂዳል፣ ፍቱንነታቸው፣ ደህንነታቸው እና ጥራታቸው የተረጋገጠላቸው የባህል መድሃኒቶች በዘመናዊ መንገድ የሚመረቱባቸውን ስልቶች ይቀይሳል፣ በጤና አገልግሎት ሥርዓት ውስጥ እንዲካተቱ የሚያስችላቸው ሃሳብ ያቀርባል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለባህል መድሃኒቶች የሚውሉ ዕፀዋቶች እንዳይጠፉ ለመጠበቅ ለሚደረጉ ሥራዎች የበኩሉን ድጋፍ ይሰጣል፤

6. <u>Powers and Duties of the Institute</u>

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ prepare national research agenda on public health and nutrition, conduct research as per the said agenda, submit policy briefs based on the research result, disseminate research findings and evaluate their impact;

2/ establish a frame work for the integration and effectiveness of researches conducted throughout the country, put in place national research database, and provide assistance to regions and other entities conducting research;

3/ produce or provide scientific assistance for local large scale production of vaccines, diagnostic kits, food science and nutritional products, and other related substances useful for the health service, through technology transfer, for major public health problems;

4/ undertake research on health system and related issues vital for health promotion and disease prevention, and evaluate impact of interventions conducted by the health sector;

5/ conduct public health research on environmental and occupational safety and health;

6/ undertake national surveys and surveillances on communicable and non-communicable diseases, nutritional problems, environmental health, health system and other health related issues;

7/ undertake research, collect and compile data on ways of preventing diseases due to malnutrition and nutritional deficiencies as well as nutritional improvement at family level;

8/ conduct research on traditional medicine and medical practices, modern drugs, study methods of production of traditional drugs whose therapeutic efficacy and safety have been proven, provide proposal to materialize their integration into the health service system, cooperate with concerned organizations for the conservation and protection of medicinal plants;

፱/ በማንኛውም የህብረተሰብ ጤና ምርምር ላይ የምርምር ተሳታፊውን ደህንነት፣ መረጃ አያያዝ፣ በአጠቃላይ የምርምር ሥነ ምግባርን እና መልካም የምርምር አሠራርን የሚመለከቱ የአፈጻፀም መመሪያዎችና ማንዋሎችን ያወጣል፤

፲/ ከአገር ውስጥና የውጭ አገር ተቋማት ጋር የጋራ ምርምሮችን ይሰራል፤ እንደአስፈላጊነቱ ምርምሮችን የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት በሌሎች አካላት አማካኝነት እንዲሰሩ ያደርጋል፤

፲፩/ በህብረተሰብ ጤና ምርምር፣ በድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥርና የላብራቶሪ ጥራት ስርዓት በሚመለከት ተጨባጭ ፍላጎቶችን መሰረት ያደረገ የአጭር ጊዜና የሥራ ላይ ስልጠናዎች ይሰጣል፣ የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎችን በመስጠት ረገድም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ይተባበራል፤ እንደአ ስፈላጊነቱም የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፪/ በተመረጡ የጤና ሥጋቶች፣ በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ በሽታዎች፣ የሥነ ምግብ ችግር እና የአካባቢ ጤና ችግሮችን በተመለከተ ቅኝት ያካሂዳል፣ ይተነትናል፣ ወቅታዊ መረጃ ያሰራጫል፤

፲፫/ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቀነስ ስልቶችን ይቀይሳል፣ የአፈጻፀም መመሪያዎችን ያወጣል፣ የዝግጁነትና የምላሽ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አቅም ይገነባል፣ ጠንካራ የቅንጅትና የትብብር ሥርዓት ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ተጋላጭነት ዳሰሳና የጤና አደጋ ሥጋት ትንተና ያካሂዳል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፬/ ወረርሽኝ ወይም ሌላ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ወይም የህብረተሰብ ጤና አደጋ ሥጋቶች ሲከሠቱ እንደአግባብነቱ በቦታው ተገኝቶ ምርመራ ያካሂዳል፣ ክስተቶችን ያረጋግጣል፣ ያነቃል፣ ያስጠነቅቃል፣ መረጃዎችን ለሚመ ለከተው አካል ያሰራጫል፣ ግብዓቶችን ያንቀሳ ቅሳል ወይም እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ ለሚደረጉ የምላሽ ሥራዎች ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፭/ ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ጤናን በተመለከተ የደረሰውን ጉዳት በማጥናት ወደነበረበት እንዲመለስ ድጋፍ ያደርጋል፤

9/ issue guidelines and manuals in all aspects of public health, on ethics and good research practice including the wellbeing, safety and record keeping of research participants;

10/ undertake joint research with concerned national and international institutions, provide financial support to other organs to undertake research as deemed necessary;

11/ provide short term and on job trainings, based on the existing critical needs on public health research, public health emergency management and quality laboratory system, collaborate with higher education institutions with respect to long term trainings, and render consultancy services as deemed necessary;

12/ conduct surveillance, analysis and disseminate current information on selected public health risks, epidemic prone diseases, and nutritional and environmental problems;

13/ design strategies, issue guidelines, develop preparedness and response plans, build capacity, establish and implement coordination and collaboration framework, conduct public health vulnerability assessment and risk analysis and provide support to prevent and mitigate public health emergencies;

14/ conduct, during epidemics or any other public health emergency or public health risk, on sight investigation when deemed necessary, verify outbreaks, issue alert, provide warning and disseminate information to the concerned organs, mobilize or cause the mobilization of resources, support the response activities carried out at weredas, zones and regional levels as deemed necessary;

15/ in collaboration with other organs, assess the health damage resulting from manmade or natural disasters and provide support for the

፲፮/ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ቀውስ የሚያስከትሉ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችን በተመለከተ ዓለም አቀፍ የጤና ህጎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፯/ የሪፈራል ዲያግኖስቲክ እና አናሌቲካል የላብራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፰/ የአገሪቱ ላብራቶሪዎች ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ የላብራቶሪ ጥራት ሥርዓትን የሚመለከቱ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ የሚያስችሏቸውን ስራዎችን ይሰራል፤

፲፱/ ለሚሰጠው የማማከር፣ ሪፈራል ዲያግኖስቲክ እና አናሌቲካል የላብራቶሪ አገልግሎቶች መንግሥት ባጸደቀው ተመን መሠረት ክፍያ ያስከፍላል፤

፳/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፳፩/ ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ አማካሪ ቦርድ፤

፪/ በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

፰. <u>የአማካሪ ቦርዱ አባላት</u>

የአማካሪ ቦርዱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

፱. <u>የአማካሪ ቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

አማካሪ ቦርዱ፡-

፩/ ኢንስቲትዩቱን በፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ሌሎች አንኳር ተቋማዊ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፤

፪/ እንደ አስፈላጊነቱ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል።

16/ implement international health regulations on grave public health emergencies having implication of international crisis;

17/ provide referral diagnostic and analytical test services;

18/ undertake activities that may enable laboratories in the country to meet national and international quality standards;

19/ charge fees for consultancy, referral diagnostic and analytical test services at the rate approved by the government;

20/ own property, enter into contract and sue and be sued in its own name;

21/ perform other related activities as may be necessary for the attainment of its objective.

7. **<u>Organization of the Institute</u>**

The Institute shall have:

1/ an Advisory Board;

2/ a Director General and, as may be necessary, Deputy Director Generals, to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

8. **<u>Members of the Advisory Board</u>**

Members of the Advisory Board, including the Chairperson, shall be appointed by the government; and their number shall be determined as necessary.

9. **<u>Duties and Responsibilities of the Advisory Board</u>**

The Advisory Board:

1/ shall advise the Institute in respect of policy, strategy and other major institutional matters;

2/ may establish different technical committees as may be necessary.

**፲. የአማካሪ ቦርዱ ስብሰባዎች**

፩/ አማካሪ ቦርዱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል፡፡

፪/ ከአማካሪ ቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የአማካሪ ቦርዱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ አማካሪ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከተውን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**10. Meetings of the Advisory Board**

1/ The Advisory Board shall meet as frequently as its function requires.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Advisory Board are present at a meeting.

3/ The decisions of the Advisory Board shall be passed by a majority vote and, in the case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Advisory Board may adopt its own rules of procedure.

**11. Powers and Duties of the Director General**

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall, subject to the general directions of the Ministry, direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Institute in accordance with the federal civil service laws and, in the case of professionals engaged in the core functions of the Institute, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the Ministry the annual work program and budget of the Institute, and implement same upon approval;

d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute.

## ፲፪. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

## ፲፫. የሂሣብ መዛግብት

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ፲፬. የተሻረ ደንብ

የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፰ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

## ፲፭. መብትና ግዴታ መተላለፍ

በደንብ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፰ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

## ፲፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር

## 12. Budget

The budget of the Institute shall be allocated by the government.

## 13. Books of Accounts

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

## 14. Repealed Regulation

The Ethiopian Health and Nutrition Research Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 4/1996 is hereby repealed.

## 15. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Ethiopian Health and Nutrition Research Institute established under Regulation No. 4/1996 are hereby transferred to the Institute.

## 16. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 15th day of January, 2014.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**